# ዶ/ር ቴድሮስ አድሃኖም ከግብፁ ፕሬዚዳንት አልሲሲ ጋር ተወያዩ

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ዶ/ር ቴድሮስ አድሃኖም ከግብፁ አዲስ ተመራጭ ፕሬዝዳንት አብዱልፈታህ አልሲሲ ጋር በካይሮ ተወያዩ፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ጽ/ቤት እንዳስታወቀው ዶ/ር ቴድሮስ በፕሬዝዳንቱ በዓለ ሲመት ላይ የተገኙ ሲሆን በተጓዳኝም ከሌሎች የግብጽ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ጋር በሁለትየሽ ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት አድርገዋል፡፡ በዚሁ ወቅት ሚኒስትሩ ከግብፁ ፕሬዝዳንት ጋር ባደረጉት ውይይት ኢትዮጵያ ከግብጽ ጋር በመተማመን ላይ የተመሰረተ ግንኙነት እንዲኖራትና በተለያዩ የትብብር መስኮች በጋራ ለመስራት ቁርጠኛ መሆኗን ገልፀዋል፡፡

ፕሬዝዳንት አልሲሲ በበኩላቸው አገራቸው ከኢትዮጵያ ጋር ለመተባበርና በመተማመን ላይ የተመሰረተ አዲስ የግንኙነት ምዕራፍ እንድትጀምር እንደሚሰሩ ዝግጁነታቸውን አረጋግጠዋል፡፡ ሁለቱ ወገኖች በተጨማሪም በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ዙሪያ የተወያዩ ሲሆን የኢትዮጵያ፣ የግብፅና የሱዳን ተወካዮች ያሉበት የቴክኒክ ኮሚቴ ውይይት እንደገና እንዲጀመር ከስምምነት ደርሰዋል፡፡ የቴክኒክ ኮሚቴ ውይይቱ በፖለቲካ ምክክር እንዲደገፍም ከስምምነት ተደርሷል፡፡

በተመሳሳይ ዶ/ር ቴድሮስ አድሀኖም ከግብፅ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሚስተር ነቢል ፋህሚ ጋር በሁለትዮሽ ጉዳዮች ላይ ተወያይተዋል፡፡ ሁለቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ኢትዮጵያና ግብፅ ግንኙነታቸውን ለማጠናከር ኢንቨስትመንት፣ ንግድና ቱሪዝምን ጨምሮ በተለያዩ መስኰች ላይ ለመተባበር ዝግጁነታቸውን ገልፀዋል፡፡ በዚህም የሁለቱ አገራት የግሉ ዘርፍ አካላትና ባለሀብቶች በትብብር የሚሰሩበት ሁኔታን ማመቻቸት እንደሚያስፈልግ አመልክተዋል፡፡ በተጨማሪም በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ እና በናይል አጠቃላይ የትብብር ስምምነት ላይ ተነጋግረዋል፡፡

ዶ/ር ቴድሮስ በካይሮ ቆይታቸው በአገራችን በቱሪዝም ዘርፍ መዋለ ነዋዩን እያፈሰሰ ከሚገኘው የAlmoez Holding Group ሊቀመንበር ሚ/ር Mostafa Almoez ጋር ተወያይተዋል:: ሚኒስትሩ በኢትዮጵያ ኢንቨስት ለሚያደርጉ ባለሃብቶች መንግስት አስፈላጊውን ድጋፍና ማበረታቻ እንደሚያደርግ አስምረውበታል፡፡ የድርጅቱ ሊቀመንበርም ለኢንቨስትመንት እንቅስቃሴያቸው በኢትዮጵያ በኩል ስለተደረገላቸው ድጋፍ ምስጋና ያቀረቡ ሲሆን የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴያቸውን ከቱሪዝም ዘርፍ በተጨማሪ በሌሎችም መስኮች ለማስፋፋት ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡

**የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር**
**ቃል አቀባይ ጽ/ቤት**
**ሰኔ 03 ቀን 2006 ዓ.ም.**